የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የፖለቲካ ፓርቲዎችና የምርጫ ሂደት አቤቱታዎች አጣሪ ጉባዔ መመሪያ ቁጥር

## 21/ 2015

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

**አንቀጽ 1. አውጪው ባለሥልጣን**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በማቋቋሚያ ዐዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1) እና የኢትዮጲያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር ዐዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 74 ንዑስ (6) እና አንቀጽ 151 ንዑስ (10) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**አንቀጽ 2. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የፖለቲካ ፓርቲዎችና የምርጫ ሂደት አቤቱታ አጣሪ ጉባዔ መመሪያ ቁጥር 21/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 3. ትርጓሜ**

1. **"ዐዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር ዐዋጅ ቁጥር 1162/2011 ነው፡፡
2. **"ቦርድ"** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡
3. **"አጣሪ ጉባዔ"** ወይም "**ጉባዔ**" ማለት በዐዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት በፖለቲካ ፓርቲ የውስጥ አለመግባባቶችን እንዲሁም በምርጫ ሂደት ለቦርዱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ የውሣኔ ሃሳብ ለቦርዱ እንዲያቀርብ የተቋቋመ የባለሞያዎች ስብስብ ነው፡፡
4. **"የምርጫ ሂደት"** ማለት የመራጭ ምዝገባ፣ የዕጩ ምዝገባ፣ የምረጡኝ ቅስቀሳ፣ የመገናኛ ብዙኃን ተደራሽነት፣ የድምፅ አሰጣጥ፣ የድምፅ ቆጠራ፣ ጊዜያዊ ውጤት ማዳመር፣ የቅሬታ አፈታት ሥርዓት እና የመጨረሻ የምርጫ ውጤት ማሳወቅን የሚያካትት ነው፡፡
5. **"የጥቅም ግጭት"** ማለት የጉባዔው አባል ለአስተያየት በቀረበው ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ወይም ከባለጉዳዮቹ ከአንዱ ጋር የትዳር ወይም ሌላ ግንኙነት ያለው ወይም የነበረው ከሆነ ወይም የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ከሆነ፣ በሙያ ሥራው ወይም በኃላፊነት ባገለገለበት

ወይም በሚያገለግልበት ቦታ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የነበረው/ያለው ወይም በጉዳዩ ላይ በተሰጡ ውሣኔዎች ተሳታፊ የሆነ/የነበረ ነው፡፡

6. **“አመልካች”** ማለት አቤቱታ አቅራቢ ወገን ነው፡፡
7. **“ተጠሪ”** ማለት አቤቱታ የቀረበበት ወገን ነው፡፡
8. በዐዋጁ የተሰጡት የቃላት ትርጉም ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 4. የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በፖለቲካ ፓርቲ አባላትና አመራር መካከል ወይም በፓርቲው አባላት እና በፓርቲው ወይም በፓርቲው አደረጃጀት/የሥራ ክፍሎች መካከል ወይም በአባላቱ መካከል በሚፈጠሩ አለመግባባቶች እንዲሁም በምርጫ ሂደት ለቦርዱ በሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 5. የፆታ አገላለፅ</u>**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በሴት ወይም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሌላኛውን ጾታ ያካትታል፡፡

**<u>አንቀጽ 6. አላማ</u>**

የዚህ መመሪያ አላማ ቦርዱ እንዲያቋቁቋም ሥልጣን የተሰጠውን የአቤቱታ አጣሪ ጉባዔ አወቃቀር እና አሰራር መደንገግ ነው፡፡ ጉባዔው በቦርዱ ሊወሰኑ የሚችሉ በፖለቲካ ፓርቲ አባላትና አመራር መካከል ወይም በፓርቲው አባላት እና በፓርቲው ወይም በፓርቲው አደረጃጀት/የሥራ ክፍሎች መካከል ወይም በአባላቱ መካከል እንዲሁም ከምርጫ ሂደት ጋር ተያይዞ የሚነሱ አቤቱታዎች በሚቀርቡበት ጊዜ ጉዳዩን በመመርመርና በማጣራት አለመግባባቶቹን ፍትሓዊና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ የውሣኔ ሀሳብ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡ ፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የፖለቲካ ፓርቲዎችና የምርጫ ሂደት አቤቱታዎች አጣሪ ጉባዔ ስለማቋቋም

**<u>አንቀጽ 7. የጉባዔው መቋቋም</u>**

የፖለቲካ ፓርቲዎችና የምርጫ ሂደት አቤቱታዎች አጣሪ ጉባዔ በዚህ መመሪያ በቦርዱ ተቋቁሟል፡፡

**<u>አንቀጽ 8. የባለሙያ ቡድኖች ስለማቋቋም</u>**

ቦርዱ እንደቀረበለት ጉዳይ አይነትና ይዘት አስፈላጊውን የባለሙያ ግብአት ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ የባለሙያ ቡድኖች ሊያዋቅር ይችላል፡፡

**አንቀጽ 9. የጉባዔው አባላት**

1. ጉባዔው በቦርዱ የሚሰየሙ ቢያንስ ሦስት አባላት ይኖሩታል። ለቦርዱ የቀረበው የምርጫ ሂደትን የሚመለከት ጉዳይ ሆኖ ውስብስብነት ያለው ሲሆን ቦርዱ እስከ አምስት የአባላት ቁጥር ያለው ጉባዔ ሊያቋቁም ይችላል።
2. ቦርዱ በሚቀርብለት አቤቱታ ይዘት ወይም አይነት ላይ በመመስረት የጉባዔው አባላት ከሕግ፣ ፖለቲካ ሳይንስ፣ አስተዳደር፣ የማህበራዊ ጥናት እና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው የሙያ ዘርፍ የተውጣጡ እንዲሆኑ ያደርጋል።
3. ቦርዱ ከሚያቋቁመው ጉባዔ አባላት መካከል አንዱ በሰብሳቢነት እንዲያገለግል ይመድባል። የጉባዔው ሰብሳቢ የጉባዔውን ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል፤የጉባዔውን የውሣኔ ሃሳብ ለቦርዱ ያቀርባል።
4. ቦርዱ የባሞያዎች ዝርዝር የሚኖረው ሲሆን፣ ይህንንም ዝርዝር በየጊዜው እየከለሰ እና አስፈላጊ ሲሆን የአቅም ግንባታ ስልጣኖዎችን እየሰጠ ያደራጃል።

**አንቀጽ 10. የጉባዔውን አባላት ስለመሰየም**

በቦርዱ የሚሰየም የጉባዔው አባል፤

1. የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ፣
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9(2) መሠረት አግባብነት ያለው ትምህርትና ልምድ ያለው፣

በመልካም ሥነ ምግባሩ የታወቀና የተመሰገነ መሆን አለበት።

**አንቀጽ 11. የጉባዔው ተግባርና ኃላፊነት**

ጉባዔው፤

1. በዐዋጁ አንቀጽ 74 ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት በፖለቲካ ፓርቲ አባላት መካከል የፓርቲውን ሕገ ደንብ አፈፃፀም እና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች አለመግባባት ተፈጥሮ ለቦርዱ አቤቱታ ሲቀርብ፣
2. በዐዋጁ አንቀጽ 151 ንዑስ አንቀጽ (10) መሠረት በምርጫ ሂደት ላይ ተዋረዱን ጠብቆ ለቦርዱ አቤቱታ ሲቀርብ፣ ጉዳዩን በመመርመርና በማጣራት ለቦርዱ የውሣኔ ሃሳብ ያቀርባል።
3. ጉባዔው ለቦርዱ የሚያቀርበው የውሣኔ ሃሳብ በምርመራ ያገኛቸውን የፍሬ ነገር፣ የማስረጃ እና የሕግ ጉዳዮች በተገቢው መጠን የሚተነትን እና የሚያብራራ መሆን አለበት።

4. ጉባዔው ምርመራውን ሲያደርግ ለምርመራው የሚረዳው ማስረጃ እና መረጃ፣ ከተገቢው አካል እንዲቀርብ እና ለጉዳዩ ጠቃሚ ናቸው የሚላቸው ሰዎች ቀርበው የምስክርነት ቃል እንዲሰጡ በዐዋጁ አንቀጽ 161 እና በዐዋጅ 1133/2011 አንቀጽ 27 መሠረት በቦርዱ በኩል ትዕዛዝ እንዲተላለፍለት ይጠይቃል።
5. ጉባዔው ተግባራቱን የሚያከናውነው አዋጁን፤ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የአገሪቱን ሕጎችና የቦርዱን መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ይሆናል።

**አንቀጽ 12. የሥራ ዘመን**

አንድ የጉባዔ አባል በአንድ ጉዳይ ላይ ወይም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ወይም ለተወሰነ ጊዜ እንዲያገለግል ሆኖ ሊመደብ ይችላል።

**አንቀጽ 13. የጉባዔው አባላት ከኃላፊነት ስለሚነሱበት ሁኔታ**

1. አንድ የጉባዔ አባል ሆኖ የተመረጠ ሰው የቀረበውን ጉዳይ በገለልተኝነት ለመመልከት የማያስችሉ የጥቅም ግጭት ወይም ሌሎች ምክንያቶች አሉ ብሎ ሲያምን ይህንኑ ለቀሪው የጉባዔው አባላትና ለቦርዱ በማሳወቅ እራሱን ማግለል አለበት።
2. ለቦርዱ የሚቀርብ አቤቱታ አመልካች ወይም ተጠሪ አንድ የጉባዔ አባል ጉዳዩን በገለልተኝነት ከማየት የሚያግደው ነገር አለ ብሎ የሚያምን ከሆነ ማስረጃውን በማያያዝ ለጉባዔው በማቅረብ አባሉ እንዲነሳለት ለመጠየቅ ይችላል ። ጉባዔው በሚሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ከሆነ ጉዳዩን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል።

**አንቀጽ 14. የጉባዔ አባላት ሥነ ምግባር**

የጉባዔው አባላት፤

1. በሥራቸው አጋጣሚ ያወቁትን ማንኛውንም ምስጢር ለሶስተኛ ወገን ያለመስጠትና የመጠበቅ፣
2. የተመራላቸውን ጉዳይ በተቻለ ፍጥነትና በተገቢ ሁኔታ በማጣራት የውሣኔ ሃሳቡን ለቦርዱ የማቅረብ፣ እና
3. በማንኛውም ሁኔታ የጉባዔውን ወይም የአባላቱን ተዓማኒነት፣ ገለልተኝነትና ነጻነት የሚጎዳ ትግባር ያለመፈጸም ግዴታ አለባቸው።

**አንቀጽ 15. የጽሕፈት ቤት አገልግሎት**

1. **ጉባዔው የቀረቡለትን ጉዳዮች የሚመረምረው፣ ባለጉዳዮችን የሚያነጋግረው፣ ምስክር የሚሰማው እንዲሁም በጉዳዮች ላይ ውይይት የሚያደርገው ቦርዱ በዋና መሥሪያ ቤት በሚያዘጋጅ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡**
2. ጉባዔው በቦርዱ ዋና መሥሪያ ቤት በቦርዱ በሚወሠነው መሠረት አስፈላጊ ድጋፍ ሠራተኛ አገልግሎት ያገኛል፡፡
3. የጉባዔው አጠቃላይ ሠነዶች ኤሌክትሮኒክ ሠነዶችን ጨምሮ የሚቀመጡት በዋናው መሥሪያ ቤት በሚዘጋጅ ቢሮ ውስጥ ይሆናል፡፡
4. የጉባዔው የሥራ ቋንቋ የቦርዱ የሥራ ቋንቋ ነው፡፡ በጉባዔው ስብሰባ ላይ የተገኙ ባለጉዳዮች የጉባዔው የሥራ ቋንቋ የማያውቁ ከሆነ ቦርዱ የትርጉም አገልግሎት ማቅረብ ከቻለ እንዲያቀርብ ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ በሚመለከተው ተከራካሪ ወገን አገልግሎቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 16. የጉባዔው አባላት የአገልግሎት ክፍያ**

1. የጉባዔው አባላት የነፃ አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ የፍትሕ ሚኒስቴር አገልግሎታቸውን እውቅና እንዲሰጠው ቦርዱ አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፡፡
2. የጉባዔው አባላት አገልግሎታቸወን በክፍያ የሚፈፅሙ በሆነ ጊዜ የአገልግሎት አበል በቦርዱ ይወሰናል፡፡
3. ለጉባዔው አባላት ክፍያ የሚፈፀም ከሆነ ክፍያውን ቦርዱ የሚፈፅም ይሆናል፤ ለዚህም የሚሆን በጀት ይይዛል፡፡
4. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት አገልግሎት ካገኘ ከሚያገኘው የመንግስት ድጋፍ ላይ ይኸው ለጉባዔ አባላት የተከፈለው ገንዘብ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ቦርዱ አቤቱታዎችን ለጉባዔው የሚመራበት ሥርዓት

### አንቀጽ 17. የፖለቲካ ፓርቲዎች አለመግባባቶችን የሚመለከት አቤቱታ አቀራረብ

1. አንድ ፖለቲካ ፓርቲ አባል፣ የፖለቲካ ፓርቲ፣ የፖለቲካ ፓርቲ እጩ፣ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ስብስብ፣ የፖለቲካ ፓርቲው የሥራ ክፍል፣ የፖለቲካ ፓርቲ ሀላፊ ወይም የግል እጩ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ኃላፊ በዚህ መመሪያ መሠረት አቤቱታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በዚህ መመሪያ መሠረት አቤቱታ ማቅረብ የሚችል ሰው ወይም አካል አቤቱታውን በህጋዊ ወኪሉ በኩል ማቅረብ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 18. የፖለቲካ ፓርቲ የውስጥ አለመግባባቶች አፈታት ስርዓት

1. ፓርቲው አቤቱታ ሰሚ አካል ስለሚቋቋምበትና አለመግባባቱ ስለሚፈታበት ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ይወስናል፡፡
2. በአንድ ፓርቲ ውስጥ አለመግባባት ሲከሰት አቤቱታው መጀመሪያ የሚቀርበው ፓርቲው ላደራጀው አቤቱታ ሰሚ አካል ነው፡፡
3. ማንኛውም ሰው ወይም አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አቤቱታውን ፓርቲው ላደራጀው በየደረጃው ላለ አቤቱታ ሰሚ አካል ሳያቀርብ በቀጥታ ለቦርዱ አቤቱታ ለማቅረብ አይችልም፡፡

### አንቀጽ 19. ለቦርዱ ስለሚቀርቡ ሠነዶች

1. በፖለቲካ ፓርቲ አባላትና አመራር መካከል ወይም በፓርቲው አባላት እና በፓርቲው ወይም በፓርቲው አደረጃጀት/የሥራ ክፍሎች መካከል ወይም በአባላቱ መካከል ባለ አለመግባባት መነሻ አቤቱታ ለቦርዱ ሲቀርብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት አመልካች በፓርቲው ወስጥ ላለው አቤቱታ ሰሚ አካል ያቀረበውን አቤቱታ፣ በአቤቱታው ላይ የተሰጠውን መልስ፣ ማስረጃዎችንና በአቤቱታ ላይ የተሰጠውን ውሣኔ ለቦርዱ ከሚያቀርበው አቤቱታ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

2. አቤቱታው ለቦርዱ የቀረበው ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ ከሆነ በየደራጀው ላሉ የምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች የቀረቡ አቤቱታዎች፣ የአቤቱታ መልሶች፣ ውሣኔዎች እና ተያያዥ ማስረጃዎች ለቦርዱ ከሚቀርበው አቤቱታ ጋር ተያይዘው ይቀርባል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱት ሠነዶች ከምርጫ ዘመን ውጪ ባለ ጊዜ ከሆነ ውሣኔው በተሰጠ በ15 ቀናት ውስጥ፣ በምርጫ ዘመን ከሆነ የነገሩን አጣዳፊነት ወይም የወቅቱን የምርጫ ሰሌዳ ባገናዘበ መልኩ በፍጥነት መሰጠት ይኖርበታል፡፡
4. በአመልካች የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታም ሆነ በተጠሪ የሚቀርብ መልስ በፅሁፍ መሆን አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 20. አቤቱታውን ስለመምራት</u>**

ቦርዱ የቀረበለትን አቤቱታ ተቀብሎ አቤቱታው ለጉባዔው መመራት አለበት ብሎ ሲያምን ጉዳዩን ወደ ጉባዔው ይመራዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 21. ምርመራ ስለመጀመር</u>**

1. ጉባዔው በቦርዱ የተመራለት ጉዳይ እንደደረሰው በአመልካች የቀረበው አቤቱታ ለተጠሪ እንዲደርሰው ያዛል፡፡
2. ተጠሪው መልሱን፣ ይደግፉኛል የሚላቸውን የሠነድ እና የሰው ማስረጃዎች ዝርዝር ያቀርባል፤ ማስረጃዎቹ በእጁ የማይገኙም ከሆነ ያሉበትን ቦታ ይገልፃል፡፡
3. ጉባዔው ተጠሪው ያቀረበውን መልስ ከተቀበለ በኋላ አመልካችና ተጠሪ ወገኖችን በቃል የሚያነጋግርበትን ቀጠሮ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ 22. ምርመራ</u>**

ጉበኤው፤

1. ተከራካሪ ወገኖችን ከማነጋገሩ በፊት መዝገቡን በሚገባ ይመረምራል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቧቸውን የሕግና የፍሬ ነገር ክርክሮች ይለያል፡፡
2. አመልካች ያቀረበውን አቤቱታና ተጠሪው ያቀረበውን መልስ ይዘት በአጭሩ ያብራራል፡፡
3. ሊብራራለት በሚፈልጋቸው ነጥቦች ላይ ተከራካሪ ወገኖችን በቃል ወይም በጽሁፍ ተራ በተራ ማብራሪያ ይጠይቃል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች የሚሰጡትን ማብራሪያ ይመዘግባል፡፡

4. ተከራካሪ ወገኖች ያልተስማሙባቸውን የሕግና የማስረጃ ነጥቦች /ጭብጥ/ ይለያል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለጉዳዩ የሚጠቅሙ ማስረጃዎች እና ምስክሮች በቦርዱ በኩል እንዲቀርቡለት ይጠይቃል።

**<u>አንቀጽ 23. ምስክሮችን ስለመስማት</u>**

1. ጉባዔው ምስክሮች እንዲቀርቡ ቦርዱን የሚጠይቅ ከሆነ ምስክሮቹ የሚቀርቡበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ የሚገልፅ መጥሪያ እንዲላክ ዝርዝሩን ለቦርዱ ያሳውቃል።
2. ምስክሮቹን የጠራው ወገን ምስክሮቹን በቅድሚያ ይጠይቃል። ሌላኛው ወገን ጥያቄ ካለው ምስክሮቹን ለመጠየቅ ይችላል። ጉባዔው በማናቸውም ጊዜ ምስክሮችን ለመጠየቅ ይችላል።

**<u>አንቀጽ 24. ሠነዶች ስለማስቀረብ</u>**

ጉባዔው ለምርመራው የሚረዱ ሠነዶች ከሚመለከታቸው አካል እንዲቀርብለት ለቦርዱ ጥያቄ ያቀርባል። ማንኛውም ማስረጃ እንዲሰጥ የተጠየቀ ሰው በዐዋጁ አንቀጽ 161 እና በዐዋጅ 1133/2011 አንቀጽ 27 በተደነገገው የመተባባር ግዴታ መሠረት የተጠየቀውን ማስረጃ ወዲያውኑ መስጠት አለበት።

**<u>አንቀጽ 25. ስለ ጉባዔው ስብሰባና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት</u>**

1. የጉባዔው አባላት ሦስት በሚሆኑበት ጊዜ ምልአተ ጉባዔ የሚሆነው ሶስቱም አባላት ሲገኙ ይሆናል። የጉባዔው አባላት አምስት በሚሆኑበት ጊዜ ሦስት አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል።
2. ከላይ በዚህ ንዑስ አንቀፅ 1 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ ለመስጠት በተቀጠረበት እለት ሁሉም የጉባዔ አባላት መገኘት ይኖርባቸዋል።
3. ጉባዔው በቀረበለት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው የውሣኔ ሀሳብ ወይም የሚደርስበት የውሣኔ ሃሳብ በአብላጫ ድምፅ የተደገፈ መሆን አለበት።
4. የተሰጠው ድምፅ በሁለቱም ወገን እኩል በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው የተስማማበት የውሣኔ ሀሳብ ለቦርዱ ይቀርባል።
5. በውሣኔ አሰጣጥ ሂደት በጉባዔ አባላት መካከል የልዩነት ሀሳብ ቢኖር ይኸው የተለየው የውሣኔ ሃሳብ በጽሑፍ ሆኖ ተፈርሞበት ለቦርድ መቅረብ ይኖርበታል።

6. ጉባዔው የሚያቀርባቸው የውሣኔ ሃሳቦች በስብሰባው ላይ የተገኙትን አባላት፣ የአቤቱታ አቅራቢዎች ወይም ወኪሎቻቸው እንዲሁም አስተያየት የሰጡ ሰዎች ሙሉ ስምና የጉዳዩን ዝርዝር እና የተሰጡ አስተያየቶችን መያዝ አለባቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 26. የውሣኔ ሃሳብ ስለሚቀርብበት ጊዜ</u>**

ጉባዔው በተመራለት ጉዳይ ላይ ቦርዱ በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የውሣኔ ሃሳቡን ማቅረብ አለበት፡፡ አቤቱታው የምርጫ ሂደትን የሚመለከት ከሆነ ቦርዱ የሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ አግባብነት ያለው የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ያገናዘበ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 27. የውሣኔ ሀሳብ ይዘት</u>**

ጉባዔው፤

1. ጉዳዩን በሚገባ ከመረመረ በኋላ ተገቢ ነው የሚለውን የውሣኔ ሃሳብ በፅሁፍ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
2. በውሣኔ ሃሳቡ ላይ በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ፣ በተጠሪው የቀረበውን መልስ፣ የቀረቡትን ማስረጃዎች ፍሬ ነገር ዋና ዋና ነጥብ፣ አመልካች እና ተጠሪ የተለያዩባቸውን የማስረጃና የሕግ ነጥብ እና ለውሣኔ ሃሳቡ መሠረት የሆነውን ማስረጃ እና ሕግ ይጠቅሳል፡፡
3. በማጣራቱ ሂደት ወንጀል ስለ መፈፀምን የሚያስረዱ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን የደረሰበት እንደሆነ ይህንኑ በውሣኔ ሃሳቡ ላይ ይገልፃል፡፡

**<u>አንቀጽ 28. የቦርዱ ውሣኔ</u>**

1. ቦርዱ በጉባዔው የተሰጠውን የውሣኔ ሃሳብ ሊያፀድቅ፣ ሊያሻሽል፣ የራሱን ውሣኔ ሊሰጥ ወይም ጉበኤው ጉዳዩን በድጋሚ መርምሮ የውሣኔ ሃሳቡን እንዲያቀርብለት ለማዘዝ ይችላል፡፡
2. ቦርዱ ውሣኔውን የሚሰጠው በፅሁፍ ነው፡፡ ውሣኔውም በይፋ ይገለጻል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 29. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት**

በዚህ መመሪያ መሠረት ቦርዱ በሚሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ጉዳዩን በሌሎች አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ሕጎች መሠረት ለፍርድ ቤት ወይም ሌላ ሥልጣን ላለው አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

**አንቀጽ 29. የመተባበር ኃላፊነት**

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የመተባበር ግዴታ አለበት።

**አንቀፅ 30. ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ሕጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ያለ ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**አንቀፅ 31. መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከፀደቀበት ነሐሴ 11 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል

አዲስ አበባ ነሐሴ 11 ቀን 2015 ዓ.ም.

ውብሸት አየለ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምክትል ቦርድ ሰብሳቢ